# ኢትዮጵያ ዩቶፒያ

ፍራንሲስ ቤከን (Francis Bacon) አዲሲቷ አትላንትስ (New Atlantis) ቶማስ ሙር (Thomas More) ደግሞ ዩቶፒያ (Utopia) ብለው የሰየሙት ይልቁንም የአውሮፓን ከመካከለኛው ዕድሜ ወደ ዘመናዊነት የሚደረገውን ሽግግር የሕዳሴ ዘመን (Renaissance) የገለጡበት እሳቤ ከታላቁ ፈላስፋ ከፕሌቶ አትላንትስ የተወሰደ ነው። በተደነቀለት ሥራው በሪፐብሊክ (The Republic) ስለ ትማያስና ክራይቲያስ (Timaeus and Critias) በገለጸው ትንታኔው፥ አንድ የአትላስ ደሴት አለ። በዚህም ሀገር የሚኖሩ ሰዎች ፍጹማውያን የሰላም ሰዎች ናቸው፤ በማለት አጉልቶ በቅኔያዊ አገላለጽ አስቀምጧል።

በርካታ ፈላስፎች ስለ ፕሌቶ አትላንትስ ልብወለዳዊ ነው የእውነት አገር አይደለም። እንዲህ ዓይነት ፍጹማዊ ሀገር የለም እያሉ ሲጽፉና ሲናገሩ፥ ሌሎች ደግሞ የፕሌቶ አትላንትስ ፊክሽናል ሳይሆን ፋክት ማለትም ልብወለዳዊ



Scanned by CamScanner

አይደለም ይላሉ። ከነዚህ መሀከል ከ412 - 485 የነበረው ታላቁ የአቴና ፈላስፋ ፕሮክለስ (Proclus of Athens)፥ ስለ ፕሌቶ ፍጹማዊት ሀገር ሲገልጽ አትላንትስ የተባለው ሀገር ፕሌቶ የገለጸው ልብወለዳዊ ሀገር ሳይሆን በእውነት የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሀገር የኢትዮጵያ ግዛት ነበረ ብሎ ተናግሯል። ይህም የኢትዮጵያ ግዛት የነበረው አትላንትስ ፍጹማዊ ሀገር ሲሆን፥ ይህም ፍጹምነት በተለይ በሕግ፣ በመንግሥትና በማኅበረሰብአዊ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ነው። ስለ ሀገሩም፥ ፕሌቶ፣ ፍራንሲስ ቤከንና ቶማስ ሙር ሌሎችም እንደገለጹት ዕረፍት ያለበት፤ ሁከት አልባ፥ መታዘዝ የነገሠበት፥ ሰዎች የሚከባበሩበት፥ የጤና ምድር ፣ የበረከት ስፍራ ፣ የሕይወት ደሴት ነው። በፕሌቶ አትላንትስ፣ በፍራንሲስ ቤከን ኒው አትላንትስ፣ በቶማስ ሙር ዩቶፒያ የተባለው ሀገር ምሥጢሩ ምድራዊ ገነት ማለት ነው። ይህ ደግሞ መጠሪያነቱ በየትኛውም መሥፈርት ለነጻይቱ ሀገር ለኢትዮጵያ ነው። ይህችም ሀገር ዛሬ ያለውን ችግር ምሳሌ ካላደረግነው በስተቀር፥ የቃል ኪዳን ሀገርና የተባረከች ምድር ለመሆኗ ማንም አይስተውም።

ዩቶፕያ ተብሎ ለተገለጠው ኢዩቶፒያ ተብሎ ለሚተነተነው ሐሳብ ናህይ የሚለውን የግእዝ ቃል አቻ ሰጥቼዋለሁ። ዩቶፕያ የሚለው አገላለጽ ልብወለዳዊ ለማድረግ፥ በማድነቅ እንዲህ ያለ ሀገር ሊኖር አይችልም ለማለት



Scanned by CamScanner

በግሪኩ ዮቶፕያ ሲሉት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢዩቶፕያ መልካም ቦታ የሚል ትርጓሜ አለው። ይህም ናህይ ሲባል የፋይድ ተቃራኒ ነው። ምድረ ፋይድ ማለት ምድረ ፍርሃት ወድንጋፄ÷ ምድረ ጎሣር ወመርገም ማለት ሲሆን÷ ሀገረ ቃየል (ቃየን) የግፈኞችና የገዳዮች ምድር ነው። ምድረ ናህይ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ ሀገሮች ሁሉ÷ አያዳላም እንጂ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ አድልቶ የፈጠራት ትመስላለች። በሺ ሺህ ዓመት ዕድሜዋ አንዳንድ ጊዜ ያጋጠማት ችግር ቢኖርም÷ ችግሩ ሁሉ ቃል ኪዳኗን ያላወቁ፤ ነጽሮ የሌላቸው የሐሳብ ትምስውና ዋግ የመታቸው ሰዎች በንጹሕ ስንዴ መካከል በበቀሉ አረሞች ምክንያት እንጂ÷ ኢትዮጵያ ምድረ ናህይ ናት።

ይህን ደግሞ ማረጋገጥ ለሚፈልግ በርካታ የታሪክ ማስረጃዎች እንደ ፀሐይ ደምቀው ለዓለም እያበሩ ናቸው። በብርሃኑ መጠቀም ለሚፈልግ ሁሉ እሙር ነው፤ የታወቀና የተገለጠ፤ እንዲሁም የተረዳ። ለምሳሌ ብጠቅስላችሁ የአሪት እምነት መሪ ሊቀ ነቢያት ሙሴ የተሰደደባትና የተማረባት÷ አስተዳደርን ያወቀባት፤ ይህ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲሆን÷ ድኅረ ልደተ ክርስቶስ በእኛው ክፍለ ዘመን በክርስትናቸው ምክንያት÷ መከራ የደረሰባቸው የክርስትና እምነት መሪዎች ተስዓቱ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳን) የተሰደዱባትና ነጻነት ያገኙባት፤ በእኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ እስልምና እየተመሠረተ በነበረበት ጊዜ



Scanned by CamScanner

የነቢዩ መሐመድ ተከታይ ከሰማንያ በላይ የሆኑ የቅርብ ዘመዶች በመሪያቸው እንደተነገራቸው እነርሱም እንደ አወቁት የፍትሕ አገር ብለው የመጡት ወደዚህች ምድረ ናህይ ኢትዮጵያ ነበር። በሕግ፣ በፍትሕ፣ በመንግሥትና በማኅበረ ሰብእ እኩልነት፣ በአስተዳደር መካነ ዕረፍት ነፃ ምድር ኢትዮጵያ ናት።

Scanned by CamScanner